## መመሪያ ቁጥር 1025/2017

# በመንግስት የምርምር ተቋማት የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች የተጠቃሚነት መብት ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ

በመንግስት የምርምር ተቋማት የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች የተጠቃሚነት መብት ፈቃድ አሰጣጥና

# አስተዳደር መመሪያ

በመንግስት የምርምር ተቋማት የሚለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች የመነሻ ዘር ተደራሽነትን በማሳደግ አርሶ/አርብቶ አደሩ አዳዲስ ከሚለቀቁ ዝርያዎች የሚገኘውን ትሩፋት ፈጥኖ ተጣቃሚ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመንግስት የምርምር ተቋማት የተለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎችን አንዱ ድርጅት ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ ሲያስተዋዉቅ ሌላው ያለ ወጪ የዘር ገበያው ላይ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ በመኖሩና ይህም በዘር አባዦች በኩል ያለውን የዝርያ የማስተዋወቅ ስራን ያዳከመ መሆኑ በግልጽ በመታየቱ፤

የግልና የመንግስት አጋርነት በማጠናከር በዘር ስርዓቱ ውስጥ ያለውን የመነሻ ዘር አቅርቦት ችግር መቅረፍ የሚቻል በመሆኑና በመንግስት የምርምር ተቋማት የሚለቀቁ የዕፅዋት ዝርያዎች ላይ ጤናማ ውድድርን ማስፈን በማስፈለጉ፤

የግብርና ሚኒስቴር በዕጽዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር 1068/2010 አንቀጽ 32/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

***ይህ መመሪያ "በመንግስት የምርምር ተቋማት የተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች የተጠቃሚነት መብት ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 1025/2017" ተብሎ*** ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡- በዕጽዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር 1068/2010 የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1/ "**መነሻ ዘር**" ማለት አራቢ፣ ቅድመ-መሥራች፣ ወይም መሥራች የዘር ትውልዶች ነው፤

2/ "**የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**" ማለት አንድ ሰው የዕጽዋት ዘር እንዲያመርትና እንዲሸጥ በተደነገገ መስፈርት መሠረት ከባለሥልጣኑ የሚሰጥ ህጋዊ ሰነድ ነው፤

3/ "**የመንግሥት የምርምር ተቋም**" ማለት በፌደራልና በክልል መንግስታት የሚተዳደሩ የግብርና ምርምር ወይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ነው፤

4/ "**ፈቃድ ሰጪ**" ማለት የመንግስት የምርምር ተቋም ሆኖ የዕፅዋት ዝርያውን በስሙ ያስመዘገበና ዝርያውን እንዲያድስ በባለስልጣኑ ሃላፊነት የተሰጠው ነው፤

5/ "**ፈቃድ ተቀባይ**" ማለት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኘ እና የፈቃድ ሰጪን የዕጽዋት ዝርያ መነሻ ዘር በተወሰነ የሥራ አካባቢ በ እንዲያባዛና እንዲሸጥ፣ ዝርያውን እንዲያስተዋውቅ እንዲሁም ለሌሎችም መብቱን በክፊል እንዲያስተላልፍ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

6/ "**የሥራ አካባቢ**" ማለት ፈቃድ ተቀባይ ፈቃድ ያገኘበትን ዝርያ እንዲሸጥ ስምምነት የተደረሰበት ቦታ ነው፤

7/ "**ባለሥልጣን**" ማለት የኢትዮጵያ የግብርና ባለሥልጣን ወይም በክልል የዝርያን እና ዘር ጥራትን ለመቆጣጠር ህጋዊ ሥልጣን የተሰጠው ተቋም ነው፤

8/ በዕጽዋት አዳቃዮች መብት አዋጅ ቁጥር 1068/2010 የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

9/ "**ጾታ**" በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም ያገለግላል።

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአገር ውስጥ ለምተው ወይም ከውጭ ገብተው በመንግስት የምርምር ተቋማት በተመዘገቡ የዕፅዋት ዝርያዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. **ዓላማ**

በመንግስት የምርምር ተቋማት የተመዘገቡትን የዕፅዋት ዝርያዎች ለፈቃድ ተቀባይ በማስተላለፍ የዘር አቅርቦትንና ተደራሽነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

5. **የፈቃድ ተቀባይ ልየታ መስፈርቶች**

ፈቃድ ተቀባዩ ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

1/ የንግድ ፈቃድ እና ከባለሥልጣኑ የታደሰ የመነሻ ዘር አባዥነት የብቃት ማረጋገጫ ያለው፤

2/ መነሻ ዘር ለማባዛት የሚያስችል የውስጥ ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ያለው መሆኑ በፈቃድ ሰጭው አካል የተረጋገጠለት፤

3/ በአራቢ ዘር ብዜት ለመሰማራት በተለይ ዘርን ከአንድ የምርት ወቅት በላይ ለማቆየት የሚያስችል የማቀዝቀዣ ስርዓት የተዘረጋለት መጋዘን ያለው፤

6. **የፈቃድ ሰጪ መብቶች**

ፈቃድ ሰጪ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1/ ፈቃድ በሚሰጠው ዝርያ ላይ የዝርያ ባለቤትነት መብቱን ከመጠቀም አያግደውም።

2/ ፈቃድ በሚሰጠው ዝርያ ላይ በውሉ መሰረት መከናወኑን የመከታተል መብት አለው፣ በውሉ መሰረት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ዘር የማያመርት ከሆነም ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል።

3/ በሥራ አካባቢ የተገደበ ወይም አገራዊ በማድረግ የብቸኛ ተጠቃሚነት መብት ሊሰጥ ይችላል።

4/ ፈቃድ ሰጪ አግባብ ከሆነ ባለሥልጣን፣ ከክልል ግብርና ቢሮ ወይም ከፈቃድ ተቀባዩ ማስረጃዎች የማግኘት መብት አለው፤

5/ ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በግልጽ ውድድር ወይም የዘር አገራዊ ስርጭት ፍትሃዊነትን ሊያረጋግጥ በሚችል ሌላ አግባብ ሊያከናውን ይችላል።

## 7. የፈቃድ ሰጪ ግዴታዎች

ፈቃድ ሰጪ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ ለፈቃድ ተቀባይ በመነሻ ዘር ብዜት አመራረት ላይ እንደ አስፈላጊነቱ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤

2/ ለፈቃድ ተቀባይ ለድቃይ ዝርያ በየዓመቱ፣ ድቃይ ላልሆነ ዝርያ በየሦስት ዓመቱ አራቢ ዘሩን በእናት ዘር የማደስ ግዴታ አለበት።

## 8. የፈቃድ ተቀባይ መብቶች

ፈቃድ ተቀባይ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1/ ፈቃድ ሲጠይቅ በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም የስራ አካባቢን ለይቶ መጠየቅ ይችላል፤

2/ ፈቃድ ያገኘበትን ዝርያ በተፈቀደለት የሥራ አካባቢ ዘሩን በብቸኝነት የመሸጥ መብት አለው፤

## 9. የፈቃድ ተቀባይ ግዴታዎች

ፈቃድ ተቀባይ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

1/ በስራ አካባቢው የሚፈለገውን ዘር መጠን ከአገራዊ የዘር ዕቅድ ጋር በተጣጣመ አግባብ በኢትዮጵያ ዘር ደረጃ መሰረት አባዝቶ የማሰራጨትና ዝርያውን የማስተዋወቅ ግዴታ አለበት፤

2/ ፈቃድ በተሰጠው ዝርያ ላይ በየዓመቱ እየጨመረ የሚሄድ የዘር ፍላጎት መፍጠር አለበት፤

3/ በአንቀጽ 7(1) ከተገለጸው የቴክኒክ ድጋፍ ጋር ተያይዞ የሚወጣውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለበት፤

4/ ለድቃይ ዝርያ በየዓመቱ፣ ድቃይ ላልሆነ ዝርያ በየሦስት ዓመቱ አራቢ ዘሩን በእናት ዘር የማሳደስ ግዴታ አለበት፤

5/ ፈቃድ ተቀባይ ለፈቃድ ሰጪ ወይም አግባብ ለሆነ ባለሥልጣን፣ ለክልል ግብርና ቢሮ እና ለፈቃድ ሰጪ የሚከተሉትን ማስረጃዎች የመስጠት ግዴታ አለበት፤

ሀ) በዝርያው የተሸፈነ ማሳ ስፋት በሄክታር እና

አድራሻ፣ ለ) የተመረተ ጥሬ ዘር መጠን፣

ሐ) ጥራቱ የተረጋገጠ የዘር

መጠን፣ መ) የሽያጭ መጠን፣

ሠ) የዝርያ ተጠቃሚዎች ግብረ-መልስ እና

ረ) እንደ አስፈላጊነቱ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ማስረጃዎች ያካትታል፡፡

10. የዝርያ እድሳት የእናት ዘር አቅርቦት

1/ በአንቀጽ 7(2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ሰጪው ለፈቃድ ተቀባዩ እናት ዘር በሽያጭ ያቀርባል፤

2/ የእናት ዘር ሽያጭ እንደየተቋማቱ የዘርና ተረፈ ምርት ሽያጭ አፈፃፀም መመሪያዎች መሰረት የሚተገበር ይሆናል፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው የእናት ዘር መሸጫ ዋጋ ትመና ዝርያውን ለማደስና ለማቆየት የሚወጣውን ወጪ የሚያካክስ ይሆናል።

11. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በግብርና ሚኒስቴር የፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር